ቁጥር / Ref. No 1/20/1/10
ቀን / Date 02 ጳጉሜ 2010

በዝርዝሩ ለተመለከቱት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ መመሪያ ስለመስጠት

ታክስ በግምት ስለሚሰላበት ሁኔታ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 138/2010 የላክንላችሁ ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ዑመር ሁሴን ኦባ
ዋና ዳይሬክተር ሚኒ...

- ለሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት
- ለኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
- ለኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት
- ለዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት
- ለፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጥናትና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለአገር ውስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ኦዲት ልቀት ማዕከል ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አስተዳደር ማጣጣምና የክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአምራቾችና የወጪ ንግድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኦዲት አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኮንትሮባንድ ክትትልና ዕቃ አወጋገድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለለውጥና የመልካም አስተዳደር ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሥልጠና ማዕከል ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለትምህርትና ሥልጠና ዳይሬክቶሬት
- ለሥልጠና ማስተባበርና ግብዓት አቅርቦት ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር
- ለአገር ዉስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር
- ለኦዲት አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር
- ለአቅም ግንባታና ሀብት አስተዳደር ዘርፍ ም/ዋ ዳ/ር ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለአገር ውስጥ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለጉምሩክ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለህግ ማስከበር ዘርፍ ም/ዋና ዳ/ር ጽ/ቤት ኃላፊ

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት
- ለምሥራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>አዲስ አበባ</u>

ለአዳማ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዳማ</u>

- ለሐዋሳ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሐዋሳ</u>
- ለባህር ዳር ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ባህር ዳር</u>
- ለመቀሌ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት
  <u>መቀሌ</u>
- ለድሬደዋ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ድሬደዋ</u>
- ለጅማ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጅማ</u>
- ለኮምቦልቻ ገ/ጉ/ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ኮምቦልቻ</u>

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## የግምት ታክስ ስሌት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 138/2010

ነሀሴ 2010 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 3

# የግምት ታክስ ስሌት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 138/2010

ትክክለኛ ገቢን አስታውቆ ታክስ መክፈል በታክስ ከፋዩ ላይ የተጣለ ኃላፊነት ሲሆን ይህንን ኃላፊነት በማይወጣ ታክስ ከፋይ ላይ የሚፈለግውን የታክስ መጠን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

ታክስ ከፋዩ ምንም ዓይነት የሒሳብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ፣ ወይም ባለስልጣኑ በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር የሂሳብ መዝገቡን ያሻሻለ እንደሆነ ፣ በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 3 መሠረት በየወቅቱ የሚታየውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና የዋጋ ግሽበት ከግምት ውስጥ በማስገባት የታክሱን ልክ በግምት ለመወሰን እንዲቻል፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 26(8) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "**የግምት ታክስ ስሌት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር..../2010**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "**የግምት ታክስ ስሌት**" ማለት ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ ሕግ መሠረት ማቅረብ የሚገባውን የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ እንደሆነ ወይም በግምት ከመወሰኑ በፊት ካላቀረበ ወይም የሒሳብ መዝገብ ሳያቀርብ ገቢውን ያስታወቀ ወይም ባለስልጣኑ በመለወጥ፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር የሂሳብ መዝገቡን ያሻሻለ እንደሆነ በማንኛውም ጊዜ የሚያገኘውን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ታክስ ከፋዩ ሊከፍለው የሚገባውን የታክስ መጠን የሚገልጽ ስሌት ነው።

Ethiopian Revenue and Customs Authority
Records & Documentation No. 3

ጊዜ ዝቅተኛው ዓመታዊ ሽያጫቸውን በመውሰድ አስቀድሞ የተወሰነ የሥራ ዘርፍ ግብር ለመወሰን የሚያስችል ስልት ነው።

3. **"ያልተጣራ ትርፍ"** ማለት ከሽያጭ ገቢ ላይ የግዢ ወጪ ብቻ በመቀነስ የሚገኝ ትርፍ ነው።

4. **"ልኳንዳ ቤት"** ማለት ለምግብነት የሚውል የበሬ፣የላም፣ የበግ፣የፍየል፣የጥጃ ወይም የእንቦሳ፣ የግመል እና የአሳማ ሥጋን በጥሬ ወይም በጥብስ መልክ ያለማባያ ወይም ከማባያ (ዳቦ፣እንጀራ፣ዳጣ ወዘተ.) ጋር የመሸጥ ንግድ ሲሆን መጠጥ መሸጥን አይጨምርም።

5. **"የኮሚሽን ንግድ"** ማለት የአንድ አምራች ወይም አስመጪ ምርትን ወይም አገልግሎትን ለገዥ ለማስተዋወቅ ወይም ለመሸጥ በሚደረግ ስምምነት መሠረት የምርቱ ወይም የአገልግሎቱ መሸጫ ዋጋ በአምራቹ ወይም በአስመጪው እየተወሰነ የኮሚሽን ጥቅም ለማግኘት የሚሰራ ሥራ ነው።

6. **"የወኪል ንግድ"** ማለት የአንድ አምራች ወይም አስመጪ ምርትን ወይም አገልግሎትን በራሱ በመግዛት የምርቱን ወይም የአገልግሎቱን የመሸጫ ዋጋ በወካዩ ወይም በተወካዩ እየተወሰነ የሚሰራ ሥራ ነው።

7. **"የሦስተኛ ወገን መረጃ"** ማለት የታክስ ከፋዩን የታክስ ግዴታን በአማራጭ መንገድ ለመወሰን የሚያገለግል የግዥ ወይም ሽያጭ መረጃ ነው።

8. **"ታክስ ያላስታወቀ"** ማለት በታክስ ህግ መሰረት የታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሰው ታክሱን በባለሥልጣኑ በተዘጋጀ የማስታወቂያ ቅጽ አማካይነት የሒሳብ መግለጫ ያላቀረበ ወይም ቅጹን ሞልቶ እና የሂሳብ መግለጫውን አዘጋጅቶ ባለማቅረቡ ባለሥልጣኑ በግምት የታክስ ስሌት ካዘጋጀ በኋላ የሚቀርብ ማለት ነው።

9. **"አልፎ አልፎ ሀብትን ማከራየት"** ማለት በንግድ ሥራ ያልተሰማራ ሰው ሀብቱ በመደበኛነት ለሌላ ዓላማ ወይም አገልግሎት የሚውል ሆኖ መደበኛ አገልግሎት በማይሰጥበት ጊዜ ብቻ የሚከራይ ሀብትን ያመለክታል።

10. **"ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን የባለሥልጣኑን ቅ/ጽ/ቤት እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ገቢዎች ባለሥልጣንን ይጨምራል።

11. **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው።

Ethiopian Revenue and Customs Authority
Records & Documentation

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

በታክስ ህግ መሠረት የታክስ ማስታወቂያ ባላቀረበ ወይም ታክሱን አስታውቆ የመክፈል ግዴታውን ባልተወጣ ወይም የታክስ ስሌት መግለጫው ተቀባይነት በማጣቱ ባለስልጣኑ በመለወጥ ወይም በመቀነስ ወይም በመጨመር ሊሻሻል የሚገባው የታክስ ስሌት መግለጫ ባቀረበ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 4. የግምት ታክስ አሠራር መርህ

**ለዚህ መመመሪያ አፈጻጸም ሲባል የታክስ ግምት አሰራር መርህ የሚባለው፡-**

1. ባለሥልጣኑ በየወቅቱ የሚታየውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና የዋጋ ግሽበት ከግምት ውስጥ በማስገባት የገቢ መጠንን በግምት ይወስናል፡፡
2. ታክስ ከፋይ በግብር ዓመቱ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ከሚወድቁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ወይም የንግድ ዘርፎች ገቢ ያገኘ እንደሆነ ሁሉም ገቢዎች ተጣምረው የሚወሰኑ ሲሆን የሠንጠረዥ "ሐ" ገቢዎች ውስጥ ከንግድ ስራ የተገኘ ገቢ እና የማዕድን ስራ ገቢ የሚጣመሩ አይሆንም፡፡
3. ጠቅላላ ገቢያቸው በባለስልጣኑ ወይም ከሶስተኛ ወገን በሚገኝ መረጃ የሚወሰንባቸው ዘርፎች፣ በቀን ገቢ ግምት፣ በቁርጥ ግብር አወሳሰን ስርዓት፣ ግብር የሚወሰን ሲሆን ከተዘረዘሩት ውስጥ ከአንድ በላይ በተመሳሳይ ወይም በተለያየ የንግድ ዘርፍ ሆኖ ገቢው በአንድ ሰንጠረዥ የሚወድቅ ገቢ ያገኘ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢው በሚወድቅበት ሰንጠረዥ መጣኔ መሰረት ግብሩ ተሰልቶ ይወሰናል፡፡
4. በቀን ገቢ ግምት የሚሰላ ከንግድ ስራ የተገኘ ገቢ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተውን የየዘርፉ የስራ ቀናት መሠረት በማድረግ የግብር ዓመቱ የሽያጭ መጠን ይወሰናል፡፡
5. ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ፣ በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ በቅድሚያ የተከፈለ ግብር እና በግብር ዓመቱ ተከፋፍሎ ለባለስልጣኑ ገቢ የተደረገ ግብር በሚቀርበው ማስረጃ መሠረት ለግብር ዓመቱ ከሚከፈለው ግብር ላይ ይቀነሳል፡፡
6. ገቢው ከተመዘገበበት የግብር ዘመን ውጪ ዘግይቶ የተቀነሰና ለባለስልጣኑ ገቢ የተደረገ የቅድመ ግብር ክፍያ በሚያስታውቅበት የግብር ዘመን የሚቀናነስ ሲሆን፣ እንዲቀናነስለት የሚያቀርብ ግብር ከፋይ የቅድመ ግብር ክፍያ ማስረጃ ከግብር ዘመኑ በፊት ለነበረው ገቢ የተቀነሰ መሆኑን በፅሑፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

7. በሀገር ውስጥ ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ በቅድሚያ የተከፈለ ግብር መጠን የግብር ከፋዩን ሽያጭ መጠን ትክክለኛነት በማረጋገጥና በማነጻጸር በሽያጭ መጠን ላይ የሚያመጣው ለውጥ ካለ ለግብር አወሳሰን ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሠንጠረዥ "ሀ"፣ "ለ" እና "መ" ገቢን በግምት ስለመወሰን

### 5. ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ገቢን በግምት ስለመወሰን

1. ከራሱ ገቢ ላይ ግብር የመቀነስ ግዴታ ያለበት ተቀጣሪን በሚመለከት፡-
   ሀ) ከቀጣሪው በሚገኝ የተቀጣሪውን የገቢ መጠን መረጃ መሰረት በማድረግ ይወሰናል፡፡
   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ የተጠቀሰውን መረጃ በሌለበት ጊዜ ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ቀጣሪ ድርጅቶች አማካይ የተቀጣሪ የገቢ መጠን በመውሰድ ይወሰናል፡፡
   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ለ የተጠቀሰው መረጃ በማይኖርበት ሁኔታ ታክስ ከፋዩ ቀድሞ ሲያሳውቅ የነበረውን መረጃ በመውሰድ ይወሰናል፡፡
2. ከተቀጣሪ ገቢ ላይ ግብር የመቀነስ ግዴታ ያለበት ቀጣሪ ቀንሶ ገቢ ያላደረገውን ወይም ሳይቀንስ የቀረውን ግብር በግምት ለመወሰን ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሰጠውን መረጃ በመጠቀም የቅጥር ገቢ ግብር ይወሰናል፡፡
3. ለሁሉም የተሽከርካሪ ዓይነት ዝቅተኛ የሾፌርና የረዳት ደመወዝ በቁርጥ የሚወሰን ሲሆን የተሳቢ ተሽከርካሪ ተጎታችና ጎታች እንደ አንድ ተሽከርካሪ የሚቆጠሩ ስለሆነ በመጫን አቅሙ የተመለከተው የሾፌርና የረዳት ደመወዝ ተወስዶ የመቀጠር ገቢ ይወሰናል፡፡
4. ከላይ የተገለፀው ንዑስ አንቀጽ 3 ቢኖርም የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪ አከራይ ታክሱ በግምት የሚወሰን ሲሆን መደበኛ የግምት ግብር አወሳሰን ሥርዓት ለሾፌርና ለረዳት ደመወዝ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

### 6. ከመቀጠር የሚገኝ መደበኛ ያልሆነ ገቢን በግምት ስለመወሰን

በአገሪቱ ፀንተው ባሉ ህጎች ከታክሱ ነጻ የተደረጉ ገቢዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው ከመቀጠር ከሚያገኘው ገቢ ላይ በዚህ አንቀጽ መሰረት በግምት ይወሰናል፡፡

1. በወሩ ውስጥ ሠራተኛው ያገኘውን የትርፍ ሰዓት ክፍያ በወሩ ከሚያገኘው ደመወዝ ላይ በመደመር ጠቅላላ በተገኘው ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሀ" በተገለፀው መሠረት ግብር ይከፈልበታል፡፡
2. የአገልግሎት ካሳ ክፍያ፣ የሥራ መፈለጊያ ክፍያ ወይም ማስጠንቀቂያ ባለመስጠት የሚሰጥ ክፍያ፣ ስንብቱ ሕጋዊ ባለመሆኑ የሚሰጥ ካሳ እና ክፍያዎችን በጊዜው ባለመፈጸም የሚከፈል ካሳ የክፍያው መጠን በስንብቱ ጊዜ ላገኘው የመጨረሻ መደበኛ ደመወዝ ተካፍሎ በተገኘው ቁጥር ልክ የተገኘው የወራት ብዛት ለእያንዳንዱ ወር ራሱን የቻለ የወር ደመወዝ ግብር አስልቶ በመደመር ግብር የሚሰላ ይሆናል፡፡

   ሀ) የወራት ብዛት = የክፍያ መጠን/የመጨረሻው ወር ደመወዝ

   ለ) ግብር = የአንድ ወር ግብር X የወራት ብዛት

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ሲሰላ ሙሉ ወራትን ከሸፈነ በኋላ የሚገኘው የአገልግሎት ክፍያ ራሱን ችሎ እንደ አንድ ወር ደመወዝ የሥራ ግብር ይታሰባል፡፡
4. የዓመት ፈቃድ፣ ጉርሻ/ቦነስ/ እና የመሳሰሉት ክፍያዎች ተጠቃለው ከተደመሩ በኋላ ለ12 ተካፍለው የተገኘው ውጤት መደበኛ ደመወዝ ላይ ከተደመረ በኋላ የሥራ ግብሩ እንዲሰላ እና የተገኘው የሥራ ግብር ክፍያ ቀደም ሲል በወር ደመወዙ የከፈለው ግብር ተቀንሶ የእያንዳንዱ 12 ወር የግብር ልዩነት በመደመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

   ሀ) ተጨማሪ የወር ገቢ = ክፍያዎች/12

   ለ) የወር ደመወዝ እና በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ የተገኘውን ውጤት በመደመር ግብር ይሰላል፡፡

   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ለ ከተሰላው ግብር በመደበኛ ደመወዝ የተከፈለ ግብር ይቀነሳል፡፡

   መ) የእያንዳንዱ 12 ወር በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሐ በተመለከተው አግባብ ተሰልቶ ይደመራል ወይም የደመወዙ መጠን አንድ አይነት ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሐ የተገኘው ውጤት በ12 ተባዝቶ ይሰላል፡፡

## 7. የቤት ኪራይ ገቢ ግብርን በግምት ስለመወሰን

የቤት ኪራይ ገቢ ግብር በግምት የሚወሰነው፡-

1. በአከራይና በተከራይ መካከል የተፈጸመ የኪራይ ውልን መሰረት በማድረግ፣
2. በንዑስ ቁጥር 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ታክስ ከፋዩ ያቀረበው ማስረጃ ተአማኒነት ከሌለው፣ ከ3ኛ ወገን መረጃ ጋር ተመሳክሮ የተሻለው ተወስዶ ግብር ሊወሰን ይችላል ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት መወሰን ካልተቻለ በተመሳሳይ የሥራ ዘርፍና ደረጃ በባለሥልጣኑ ኦዲት የተደረገ ታክስ ከፋይ መረጃን ወይም በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት ወቅታዊ የገበያ ዋጋን ለመወሰን ቤቶቹ ከሚገኙበት አካባቢ በአካል በመገኘት አካባቢያዊ የገበያ ሁኔታ በማጥናት ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ደረጃ ያላቸው እንደየከተማው ደረጃ ከሁለት እስከ ሦስት ቤቶች ወርሃዊ የኪራይ አማካይ ዋጋ በመውሰድ ግብሩን ለመወሰን መሠረት አድርጎ መጠቀም ይቻላል፡፡
4. ቤቱ የተከራየው ከመኖሪያ አገልግሎት ውጭ በሚሆንበት ጊዜ ለኪራይ ገቢ የግምት አወሳሰን ጥቅም ላይ የዋለው የገቢ መጠን እንደአግባብነቱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን መሠረት በመሆን ሊያገለግል ይችላል ፡፡
5. የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋይ ግብሩ በግምት በሚሰላበት ጊዜ ከግብር ዓመቱ ጠቅላላ የኪራይ ገቢው 35% እንደ ወጪ ተይዞ 65% ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሆኖ በሠንጠረዥ "ለ" መሠረት ይሰላል፡፡
6. የደረጃ "ሀ" እና "ለ" የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ከፋይ የሆነ ግብሩ በግምት የሚሰራ ከሆነና ከአንድ ዓመት በላይ የሚሸፍን የኪራይ ክፍያ የተቀበለ እንደሆነ የኪራይ ገቢው በግብር ዘመኑ ተጠቃሎ ተይዞለት ግብሩ ገቢው ለሚሸፍናቸው ዓመታት ተሸንሽኖ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መጣኔ መሰረት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 በተመለከተው መንገድ ከአንድ ዓመት በላይ የሚቆይ የኪራይ ውል የውል ዘመኑ ከማለቁ በፊት የተቋረጠ እንደሆነና ለተከራይ ቀሪ ክፍያ መመለሱ በማስረጃ ሲረጋገጥ በብልጫ የከፈለው ታክስ ተሰልቶ ሊመለስለት ወይም ለቀጣይ የግብር ዘመን ታክስ ከፋዩ በጽሁፍ ፍላጎቱን ሲገልጽ በታሳቢነት እንዲያዝለት ይደረጋል፡፡

**8. ሀብትን እልፍ እልፍ በማከራየት የሚገኝ ገቢ በግምት ስለመወሰን**

ሀብትን እልፍ እልፍ በማከራየት የሚገኝ ገቢ ላይ በግምት የሚወሰነው፡-

1. በባለስልጣኑ ኢንተሊጀንስ ወይም በተባባሪ አካላት ወይም በጥቆማ ከሶስተኛ ወገን የሚገኝ መረጃን በመጠቀም ሊወስን ይችላል፡፡
2. አልፎ አልፎ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ሀብት የሚያከራይ ግብር ከፋይ የገቢ መጠን መሰረት በማድረግ ሊወስን ይችላል፡፡
3. ለንዑስ አንቀጽ 2 አፈፃፀም ሀብቱ የሚገኝበት አካባቢ እና የታክስ መረጃ ሥርዓት መሰረት የሚገኝ መረጃ በመጠቀም ሊወስን ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተመለከቱት መንገዶች የሚገኝ መረጃ በቅደም ተከተል መሠረት እየተወሰደ ለታክስ ውሳኔው ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሠንጠረዥ "ሐ" ገቢን በግምት ስለመወሰን

### 9. የሠንጠረዥ "ሐ" ገቢ በግምት ስለሚወሰንበት ሁኔታ

1. ለታክስ ውሣኔ መሠረት የሚሆነው የሽያጭ ገቢ መጠን በግምት የሚወሰነው፡-

ሀ) ስለ ታክስ ከፋዩ ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ታክስ ከፋዩ ያቀረበውን የሽያጭ መረጃ ወይም ከሦስተኛ ወገን መሠረት በማድረግ፣

ለ) ስለ ታክስ ከፋዩ ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የግዢ መጠን ከታክስ ከፋዩ ወይም ከሦስተኛ ወገን መረጃ የተገኘ እንደሆነ የተገኘውን የግዢ መረጃ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተውን ያልተጣራ የትርፍ መቶኛን ተጠቅሞ ወደ ሽያጭ በመቀየር፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ለፊደል ተራ ለ አፈፃፀም ጥቅም ላይ የሚውለው ቀመር የሚከተለው ይሆናል፤

$$ሽያጭ = 100\left\{\frac{ግዥ \times 100}{ያልተጣራ\ የትርፍ\ መጣኔ}\right\}$$

መ) ከሦስተኛ ወገን መረጃ ሊገኝ በማይችልበት ሁኔታ ለታክሱ ስሌት መሠረት የሚሆነው ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ

ከሚከፈልበት የሒሳብ ወር ወይም ቀጥተኛ የሆነ ታክስ ከሚከፈልበት የሒሳብ ዓመት በፊት ታክስ ከፋዩ ለከፈለው ታክስ መሠረት በሆነው ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ መጠን ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጠቀሱት መንገዶች የታክስ ከፋዩን ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ለመወሰን ካልተቻለ፡-

   ሀ. በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ ከሚገኝ ከታክስ አወሳሰን እና ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ቁጥጥር ቡድኖች የተዋቀረ ቢያንስ ሦስት አባላት ያሉት የገቢ ጥናት ኮሚቴ ታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት አካባቢ በአካል በመገኘት አካባቢያዊ የገበያ ሁኔታ ያጠናል፡፡

   ለ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የሚደረግ ጥናት ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የንግድ ዓይነትና ደረጃ ያላቸው እንደየከተማው ደረጃ ከሁለት እስከ ሦስት ንግድ ቤቶች ያስታወቁትን ወይም የተወሰነባቸውን ዓመታዊ አማካይ ጠቅላላ ገቢ በመውሰድ ያዘጋጀው አማካኝ የቀን ገቢ መረጃ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ ወይም ለወከለው ኃላፊ ቀርቦ ሲጸድቅ ለታክስ አወሳሰን የሚያገለግል ይሆናል፡፡

3. ታክስ ከፋዩ በባለሥልጣኑ በተደረገ ክትትል ለግብይት ደረሰኝ ባለመስጠት ይህ መመሪያ ከጸናበት ጊዜ ጀምሮ በሚያዝ ሪከርድ በአንድ የግብር ዓመት ሶስት ጊዜ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው እንደሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ 2 በተገለጸው መንገድ ታክሱ ይወሰናል፡፡

4. ለዚህ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 አፈፃፀም የታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራን በአካል ተገኝቶ ስለገቢው በሚጠናበት ወቅት የሚከተሉት ጉዳዮች ታሳቢ መደረግ አለባቸው፡፡

   ሀ.የንግድ ሥራው ያለበት አካባቢ ለንግዱ ሥራ ያለው አመቺነት፣ እንዲሁም የንግድ እንቅስቃሴውን ማገናዘብ፤

   ለ.የድርጅቱ ሠራተኞች ብዛት እና የሚከፈላቸውን የደመወዝ መጠን፤

   ሐ.የንግድ ሥራው የሚሰራበት ቤት የኪራይ መሆን አለመሆኑንና የኪራይ ከሆነ የኪራይ መጠን፤

   መ.የድርጅቱን የመብራት፣ የውኃ እና የስልክ ፍጆታ ወጪ፤

ሠ.ስሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1-3 የተመለከቱት ስልቶች በቅደም ተከተል ጥቅም ላይ የሚውሉ ሆኖ ለደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ጥቅም ላይ የሚውል የተጣራ የየንግድ ዘርፍ ትርፍ መጣኔን ለአወሳሰን ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡

6. በዚህ ንዑስ አንቀጽ 4 ተሰልቶ የተገኘውን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ በሠንጠረዥ "ሐ" የግብር መጣኔ መሠረት ተሰልቶ ይወሰናል፡፡

7. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በተመለከተው የግምት አወሳሰን ጥቅም ላይ የዋለው የሽያጭ መጠን እንደአግባብነቱ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ለተርን ኦቨር ታክስ የግምት አወሳሰንም መሠረት በመሆን ያገለግላል፡፡

8.በዚህ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የታክስ ከፋዩን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በአካል ተጠንቶ በተገኘ መረጃ መሠረት ታክሱ የተወሰነ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲሰላ ታክስ የተከፈለበት ግዢ ማስረጃ ላይ የተገለጸው የግብዓት ታክስ ይቀናነሳል፡፡

9.ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ 1-8 የተዘረዘሩት ግብርን በግምት የመወሰን ስልቶች ለግለሰብም ሆነ የህግ ሰውነት ላላቸው ታክስ ከፋዮች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

10. **መደበኛ የግምት አወሳሰን** /Standard Assesement/

የሚከተሉት የንግድ አገልግሎቶች ከዚህ በታች በተገለፁት በመደበኛ የግምት አወሳሰን መሰረት በግምት የሚወሰን ይሆናል፡፡

1. **የወፍጮ ቤት አገልግሎት ንግድ**
   ሀ) ከአንድ በላይ ቋት ያለው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለማስላት ለቋቱ የተመለከተውን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ መጠን በቋቱ ብዛት መሠረት ተደርጎ ግብሩ የሚወሰን ይሆናል፡፡
   ለ) የየቋቱ የምርት ዘመን የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ የምርት ዘመናቸው በተመሳሳይ ምድብ ውስጥ የሚወድቁ ቋቶችን ሽያጭ መደመር እና በተለያየ የምርት ዕድሜ ምድብ የሚገኙትን ቋቶች ግብር የሚከፈልበትን ገቢ በማጣመር ግብሩን መወሰን ይገባል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ እና ለ ላይ በተገለጸው መሠረት ተሰልቶ የተገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሠንጠረዥ "ሐ" የግብር መጣኔ መሠረት ግብሩ ተሰልቶ ይወሰናል፡፡

2. **የተሽከርካሪ ትራንስፖርት አገልግሎት ንግድ**

1.የትራንስፖርት ንግድ ሥራ ግብር የሚወሰነው ተሽከርካሪው የተመረተበት ዘመን መሠረት ተደርጎ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ.የህዝብ ማመላለሻ የሆኑ ትራንስፖርት ዓይነቶች በመቀመጫ ወንበር ብዛት፤

ለ. የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት ዓይነቶች በጭነታቸው መጠን (በኩንታል) ፤

ሐ.የፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት ዓይነቶች በሚይዙት የፈሳሽ መጠን (በሊትር) ፤

መ. የተሳቢ ተሽከርካሪ የመጫን አቅም የሚወሰነው የጎታችና የተጎታች የመጫን አቅም ተደምሮ እንደ አንድ ተሽከርካሪ ተቆጥሮ፤

ሠ. የጎታች ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ለብቻውን ሲሆን የመጫን አቅሙ በሊብሬው ላይ በተገለጸው መሠረት ሲሆን በሊብሬው ላይ የመጫን አቅሙ ያልተገለጸ እንደሆነ ከዚህ በታች የተመለከተውን ቀመር መሠረት በማድረግ የተሽከርካሪ የአክስል ክብደት የመጫን አቅሙ ተደርጎ ተወስዶ፤

ለዚህ ንዑስ አንቀድ ፊደል ተራ ሀ (5) አፈጻጸም፡-

**"አክስል"** ማለት የተሽከርካሪ ጎማ ታስሮበት የሚዞር የብረት ዘንግ ነው፡፡

**"የአክስል ክብደት"** ማለት በተሽከርካሪ ሊብሬ ላይ የተገለጸውን መረጃ መሠረት በማድረግ ከተሽከርካሪው ጠቅላላ ክብደት ላይ ነጠላ ክብደትን በመቀነስ የሚገኝ ውጤት ነው፡፡

**"የመጫን አቅም"** ማለት በኪሎ ግራም የሚገለጸውን የተሽከርካሪ የአክስል ክብደትን ለ100 በማካፈል በኩንታል የሚገለጽ ውጤት ነው፡፡

$$\text{የመጫን አቅም} = \frac{\text{የአክስል ክብደት (ጠቅላላ ክብደት - ነጠላ ክብደት)}}{100}$$

ፈ.ተጎታቹ የተሽከርካሪ አካል ለብቻው ሲሆን በሊብሬ ላይ የተገለጸው መጠን ተወስዶ የገቢ ግብሩ በመደበኛ የግምት ግብር ይወሰናል፡፡

2.የእያንዳንዱ ትራንስፖርት ዓይነት ዓመታዊ ገቢ፣ የተጣራ ገቢና የግብር መጠን ስሌት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው በቁርጥ ግብር ሠንጠረዥ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል።

3.ዓይነታቸውና የምርት ዘመናቸው የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ያሉት ታክስ ከፋይ በየተሽከርካሪው የተገኘ ገቢ ተደምሮ የሚገኘው ጠቅላላ ገቢ በማትረፊያ ህዳግ እየተሰላ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ጋር የሚደረስበት ይሆናል።

4.በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "3" ላይ በተገለፀው መሰረት ከአንድ በላይ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ያለው ግብር ከፋይ ግብር የሚከፍልበት ገቢ ተደምሮ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብሩ የሚሰላ ይሆናል።

5. የተሽከርካሪው የግብር ዓመቱ ከፊል ጊዜ ብቻ ስራ ላይ መዋሉ ከተረጋገጠ ከዓመት ገቢው ላይ በወራቱ ተሰልቶ ግብር እንዲከፍል ይደረጋል።

6. የተሽከርካሪ ባለንብረት ራሱ የሚያሽከረክር ከሆነ ለሾፌር ይከፈል የነበረውን የደመወዝ ዓመታዊ ግብር ከተሽከርካሪ ዓመታዊ ግብር ጋር ተደምሮ ግብሩ ይከፍላል።

7.የተሽከርካሪ ዓመታዊ ግብር በሚከፈልበት ጊዜ የረዳትና የሾፌር ከመቀጠር የሚገኘው ገቢ በአንድነት የሚከፈል ይሆናል።

3. **የእርሻ አገልግሎት ተሽከርካሪ ንግድ**

ሀ) ለእርሻ አገልግሎት የሚውል ተሽከርካሪ ንግድ ሥራ ግብር የሚወሰነው ተሽከርካሪው የተመረተበት ዘመን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

ለ) የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ዓይነት ዓመታዊ ገቢ፣ ግብር የሚከፈልበት ገቢና የግብር መጠን ስሌት ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው በቁርጥ ግብር ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፣

ሐ) ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 በፊደል ተራ ሐ፣ መ፣ ሠ፣ ረ እና ሰ ላይ የተመለከቱት ለዚህ ንዑስ አንቀጽም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

4. **የኮንስትራክሽን መሣሪያ ኪራይ**

ሀ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት ታክሳቸው በግምት የሚወሰነው የኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለቤትነት (ሊብሬ) በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አማካይነት የተሰጠውና ለኮንስትራክሽን ሥራ የሚከራይ ተብሎ የተገለጸ መሳሪያ ነው።

ለ) የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪ አከራይ ታክሱ በግምት የሚወሰነው ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገውና ለትራንስፖርት ተሽከርካሪ እንዲያገለግል እንደየተሽከርካሪው የመጫን አቅም የተመለከተውን በመደበኛ የግምት ግብር አወሳሰን ሥርዓትን መሰረት በማድረግ ይሆናል።

ሐ) የኮንስትራክሽን መሣሪያ አከራይ ዝቅተኛ ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ በተመለከተው መሰረት ግብሩ በግምት በሚወሰን ታክስ ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ይደረጋል።

| ተ.ቁ | የማሽነሪው ዓይነት | የማሽነሪው ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ በዕድሜ በብር | |
|---|---|---|---|
| | | ከተፈበረከ እስከ 10 ዓመት የሆነው | ከተፈበረከ ከ10 ዓመት በላይ የሆነው |
| 1 | ኤክስካቬተር | 422,400 | 211,200 |
| 2 | ሎደር | 373,120 | 186,560 |
| 3 | ግሬደር | 485,760 | 242,880 |
| 4 | ሮለር | 253,400 | 126,720 |
| 5 | ዶዘር | 563,200 | 281,600 |
| 6 | ሩሎ | 399,872 | 199,936 |

መ) ከአንድ በላይ የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪዎች ወይም የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አከራይ የሆነ ግብር ከፋይ ለየመሣሪያው የተመለከተውን ዓመታዊ ገቢ መጠን ተወስዶ እንደአግባብነቱ ያለውን የማትረፊያ ህዳግ (የትርፍ መተመኛ መቶኛ) መሠረት በማድረግ ግብር የሚከፈልበት ገቢ መሰላት አለበት።

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ መ መሠረት ተሰልቶ የተገኘው ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሠንጠዥ "ሐ" የግብር መጣኔ መሠረት ግብር ተሰልቶ ይወሰናል።

ረ) የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ወይም ተሽከርካሪ ከ3ኛ ወገን ማስረጃ ማግኘት ከተቻለ መረጃው ተወስዶ ግብሩ ይወሰናል።

ሰ) የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪ ወይም ማሽነሪ የሚያከራይ ታክስ ከፋይ እንደአግባብነቱ የተርን ኦቨር ታክስ ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈል የሚጠበቅበት

በመሆኑ ለማሸነሪው ወይም ለተሽከርካሪው የተቀመጠ ዓመታዊ የሽያጭ ገቢ መሠረት በማድረግ እንደአግባብነቱ የተርን ኦቨር ታክስ ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ ይወሰናል፡፡

## 5. የልኳንዳ ንግድ

ሀ) በልኳንዳ ንግድ የተሰማራ ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ፣ የዕርድ አገልግሎት የተሰጣቸውን የዕርድ ከብት ዓይነትና ብዛት የዕርድ አገልግሎት ከሚሰጥ ሰው በሚያቀርበው መረጃ መሠረት የሚሰላ ይሆናል፡፡

ለ) የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት፣ የቀበሌ መዝናኛ፣ የሠራተኛ ክበብ ውስጥ የሚገኝና በአነስተኛ ደረጃ የሚመደብ ልኳንዳ ቤት ከነማባያ ወይም ያለማባያ ለተጠቃሚ የሚያቀርበው አነስተኛ የሆነ ከብት ለመብልነት የሚውለው የስጋ መጠን ለበሬ 84 ኪሎ ግራም፣ ለፍየል 10 ኪሎ ግራም እና ለበግ 8 ኪሎ ግራም እንደሆነ ተቆጥሮ እንደየከብቱ ዓይነት በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት በባለሥልጣኑ በወቅታዊ አማካኝ የአንድ ኪሎ ሥጋ የገበያ ዋጋ ተሰብስቦ በሚወሰነው መሠረት የሚሰላ ይሆናል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ለ የተገለጸው ውጭ የሚገኙና በመካከለኛ ደረጃ የሚመደቡ ልኳንዳ ቤቶች ከነማባያ ወይም ያለማባያ ለተጠቃሚዎች የሚያቀርቡት የከፍተኛ፣ መካከለኛ እና አነስተኛ የሆነ ከብት ለመብልነት የሚውለው የስጋ መጠን አማካይ ለበሬ 122 ኪሎ ግራም፣ ለፍየል 16 ኪሎ ግራም እና ለበግ 9 ኪሎ ግራም እንደሆነ ተቆጥሮ እንደየከብቱ ዓይነት በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት በባለሥልጣኑ በወቅታዊ አማካኝ የአንድ ኪሎ ሥጋ የገበያ ዋጋ ተሰብስቦ በሚወሰነው መሠረት የሚሰላ ይሆናል፡፡

መ) የግመል ሥጋን በልኳንዳ ደረጃ የሚነግድ ታክስ ከፋይ በከፍተኛ ደረጃ የሚገኝ በሬ ለመብልነት የሚውልውን የስጋ መጠን 173 ኪሎ ግራምን በመውሰድ በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት በባለሥልጣኑ እየተሰበሰበ በሚወጣው በወቅታዊ አማካኝ የአንድ ኪሎ የግመል ሥጋ የገበያ ዋጋ የሚሰላ ይሆናል፡፡

ሠ) የጥጃ ወይም እንቦሳ ሥጋን በልኳንዳ ደረጃ የሚነግድ ታክስ ከፋይ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ ለመብልነት የሚውለውን የሶስት ፍየል የስጋ መጠን 48 ኪሎ ግራምን በመውሰድ በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት በባለሥልጣኑ እየተሰበሰበ በሚወጣው በወቅታዊ አማካኝ የአንድ ኪሎ የጥጃ ወይም እንቦሳ ሥጋ የገበያ ዋጋ የሚሰላ ይሆናል፡፡

ረ) የአሳማ ሥጋን በልኳንዳ ደረጃ የሚነግድ ታክስ ከፋይ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ የሁለት ፍየል ለመብልነት የሚውልውን የስጋ መጠን 32 ኪሎ ግራምን በመውሰድ በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት በባለሥልጣኑ እየተሰበሰበ በሚወጣው በወቅታዊ አማካኝ የአንድ ኪሎ የአሳማ ሥጋ የገበያ ዋጋ የሚሰላ ይሆናል፡፡

## 6. የውጭ ሀገር አሠሪና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ

የውጭ አገር አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ስራ የሚሰሩ ሰዎች በሦስተኛ ወገን መረጃ መሠረት ተደርጎ ግብር የሚወሰንላቸው በሚከተለው መንገድ ይሆናል፡-

ሀ) ስለዘርፉ የሥራ እንቅስቃሴ ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎችን ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ፣ ከአየር መንገድ፣ ከኢንሹራንስ፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከውጭ ጉዳይና ከሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት መረጃውን በማሰባሰብ ለዘርፉ በተቀመጠው የትርፍ መተመኛ መቶኛ መሰረት ግብር እንዲወሰን ይደረጋል፡፡

ለ) በአሠሪ ሀገራት ተከፋይ የሚሆነውን የገንዘብ መጠን መረጃ በየግብር ዘመኑ ተለይቶ ለግብር አወሳሰኑ ጥቅም ላይ የሚውልበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ስምሪት አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች በየሀገሩ የላኳቸውን ሠራተኞች ብዛት በየግብር ዘመኑ በመለየት በእያንዳንዱ ተጓዥ ዝቅተኛ የአገልግሎት ክፍያ እንደየሀገሩ ከሚመለከተው አካል በሚገኝ መረጃ በመውሰድ ይሰላል፡፡

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀፅ በተመለከተው በመረጃ ላይ የተመሠረተ የገቢ መጠን ለተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን መሠረት ይሆናል፡፡

## 11. የንግድ ዘርፍ የማትረፊያ መጣኔ

1. በመንግስት የመግዣና መሸጫ ዋጋ በተተመነ የንግድ ዘርፍ (ስኳር፣ ፓልም ዘይት፣ ዱቄት፣ ጨው፣ ዳቦ እና ጠዘተ.) የተሰማራ ታክስ ከፋይ በመንግስት በተወሰነለት አካባቢ እና ዋጋ ስለመሸጡ የሚገልጽ ደረሰኝ እና የምደባ መረጃ ያቀረበ እንደሆነ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተወሰነበት የትርፍ ህዳግ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተደርጎ በመውሰድ ግብሩ ይሰላል፡፡
2. የዳቦ ቤት የሽያጭ መጠን ለማስላት በንግድ ሚኒስቴር በተደረገው ጥናት መሠረት 1 ኩንታል ዱቄት 1,000/አንድ ሺ.ህ/ ባለ100 ግራም ዳቦ(አማካይ የዳቦ መጠን) ተወስዶ ለዳቦ ቤቱ ከመንግስት አካል የተሰጠው የኩንታል ብዛት መረጃ በመውሰድ

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት የአንድ አማካይ ዳቦ(ባለ100 ግራም) ወቅታዊና አማካይ የገበያ ዋጋን በመጠቀም ይወስናል።

3. በኮሚሽን ንግድ የተሰማራ ታክስ ከፋይ ጠቅላላ ገቢ ተደርጎ የሚወሰደው በኮሚሽን ስምምነት መሠረት በየምርት ወይም በአገልግሎት የሽያጭ ዋጋ ላይ የተጨመረ ወይም ከጠቅላላ ምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ በመቶኛ የተወሰነው መጠን ይሆናል።

4. በአከፋፋይነት ወይም በጅምላ ንግድ የተሰማራ ታክስ ከፋይ፦

   ሀ) ከአምራች ጋር የተገባ የትርፍ ህዳግን የሚገድብ የጽሁፍ ስምምነት ሲኖር በስምምነቱ መሠረት ታክሱ ሊወሰን ይችላል።

   ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ የተገለጸው ስምምነት በማይኖርበት ወይም የግብይቱን መጠን የማይገልጽ በሚሆንበት ጊዜ ታክስ ከፋዩ በሚገኝበት አካባቢ የሚገኙ ወይም በባለሥልጣኑ ዘንድ መረጃቸው የሚገኝ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ በሆነ ሥራ የተሰማሩ ከሁለት እስከ ሦስት ታክስ ከፋዮች ያስታወቁት ወይም የተወሰነባቸውን መረጃ በመጠቀም ታክሱ ሊወሰን ይችላል።

   ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ እና ለ የተገለጸው መረጃ በማይኖርበት ጊዜ የታክስ ከፋዩ ጠቅላላ ገቢ በአዋጁ አንቀጽ 3 መሰረት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ተወስዶ ግብር የሚከፈልበት ገቢውን በማግኘት ሊወሰን ይችላል።

5. ታክስ ከፋዩ ምርቱን ሙሉ በሙሉ ለቸርቻሪዎች ብቻ የሚሸጥ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ ሲገኝ በፌዴራል ገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 መሠረት ለደረጃ "ሐ" ታክስ ከፋዮች የተቀመጠው የትይዩ ዘርፍ የትርፍ ህዳግ (50%) ተወስዶ የሚሰራ ይሆናል።

6. ታክስ ከፋዩ ምርቱን ለቸርቻሪዎች እና ለሸማች የሚሸጥ መሆኑ የሚገልጽ መረጃ ሲገኝ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 መሠረት ለደረጃ "ሐ" ታክስ ከፋዮች የተቀመጠው የትይዩ ዘርፍ የትርፍ ህዳግ 75% ተወስዶ የሚሰራ ይሆናል።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም ከመንግስት ባለበጀት ተቋም ጋር የትርፍ ህዳግ ተወስኖ በሚከናውን ዕቃ ግዥ ወይም የአገልግሎት (ግንባታ፣ ስልጠና፣ ጥናት እና የመሳሰሉት) የአቅራቢው ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚወሰነው በግዥ ውል የተገለጸውን የትርፍ ህዳግን በመውሰድ ይሆናል።

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ከተገለጸው ውጭ የሚደረግ ግብይት የአቅራቢውን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን በመደበኛ የትርፍ ህዳግ የሚሰላ ይሆናል።

9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 እና 6 በተገለጹ ግብይቶች ገቢ ያገኘ ታክስ ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተጣምሮ ታክሱ ይሰላበታል።

## 12. የጥቃቅን ኢንተርፕራዝን ታክስ በግምት የሚወሰንበት ሁኔታ

1. ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500 ሺህ በታች የሆነ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከሦስተኛ ወገን በሚገኝ መረጃ ወይም አማካይ ቀን ገቢ ተገምቶ የሚወሰን ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መንገድ የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ከፌደራል ገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ጋር አባሪ በተደረገው የደረጃ "ሐ" ታክስ ከፋይ በትይዩ የሚገኝ የንግድ ዘርፍ ማትረፊያ መጣኔ ተወስዶ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ይወሰናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-
   ሀ) የትርፍ ህዳጉ በመንግስት በሚወሰን የንግድ ዘርፍ የተሰማራ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ከሆነ የትርፍ ህዳጉ በሚመለከተው የመንግስት ተቋም የተወሰነው የትርፍ ህዳግ ተወስዶ ወይም፣
   ለ) ለባለበጀት የመንግስት ተቋም የትርፍ ህዳጉ የተገደበ የጽሁፍ ስምምነት መሠረት በማድረግ ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚያቀርብ ሲሆን በስምምነቱ የተወሰነው የትርፍ ህዳግ ተወስዶ ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚወሰን ይሆናል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተገለጸው ውጭ የሚደረግ ግብይትን የአቅራቢውን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን በመደበኛ የትርፍ ህዳግ የሚሰላ ይሆናል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢ ከብር 500 ሺህ ወይም አንድ ሚሊዮን በላይ ሆኖ ገቢውን በሒሳብ መዝገብ ያላስታወቀ ወይም የሒሳብ መዝገብ ያላቀረበ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የግምት ታክስ አወሳሰን ሥርዓቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

13. የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የታክስ ማስታወቂያ ጊዜ

1. ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500 ሺህ በታች የሆነ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የንግድ ትርፍ ግብሩንና የተርን ኦቨር ታክሱን በታክስ ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በአንድነት ማስታወቅ አለበት፡፡
2. ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500 ሺህ በላይ ሆኖ ከ 1 ሚሊዮን በታች የሆነ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የንግድ ትርፍ ግብሩ በታክስ ዓመቱ ወይም በድርጅቱ የሂሳብ አመት በተጠናቀቀ በሁለት ወራት ውስጥ እንዲሁም የተርን ኦቨር ታክሱን በየሦስት ወሩ ማስታወቅ አለበት፡፡
3. ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 1 ሚሊዮን በላይ የሆነ ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ የንግድ ትርፍ ግብሩ በታክስ ዓመቱ ወይም በድርጅቱ የሂሳብ አመት በተጠናቀቀ በአራት ወራት ውስጥ ፣ እንደአግባብነቱ የተርን ኦቨር ታክሱን ወይም የተጨማሪ እሴት ታክሱን በየወሩ ማስታወቅ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ስህተትን ስለማረም

14. የሚታረም የታክስ ስህተት

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በአዋጁ አንቀጽ 85 መሰረት የሚታረም የታክስ ስህተት የሚባለው፡-

1. የመደመር፣ የመቀነስ፣ የማባዛትና የማካፈል ስህተት፣
2. በስሌት ማጠቃለያ ላይ ከመንደርደሪያ ሀሳብ መለየት ወይም መቃረን፣
3. ከአንድ የሂሳብ ቁጥር ከፊት ወይም ከኋላ የቁጥር መጨመር ወይም መቀነስ ወይም የሒሳብ ቁጥር ቦታ መቀያየር (transposition)፣
4. የገቢ ወይም የወጪ ክድ አመዘጋገብ ስህተት፣
5. የቃል ወይም የሐረግ በአዎንታ ወይም አሉታ መቀያየር፣
6. የሒሳብ ቁጥር ወይም ሀሳብ መተው ወይም መዘለል (omission)፣

7. ከግብር ነጻ የሆነ ገቢን ግብር በሚከፈል ገቢ ውስጥ መጨመር፣

8. በአንድ ታክስ ከፋይ ሒሳብ ውስጥ የሌላ ታክስ ከፋይ ሂሳብ መጨመር ወይም ማቀያየር፣

9. የታክስ መጣኔን ወይም የትርፍ ህዳግን መሳሳት፣

10. በታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል፣ በታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲስተካከል የተወሰነን ጉዳይ አለማስተካከል፣

11. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1-10 የተዘረዘሩትን መሰል የሚታረም ስህተት ዝርዝርን ባለሥልጣኑ በሰርኩላር ለመግለጽ ይችላል።

12. በዚህ አንቀጽ መሠረት ስህተት ሊታረም የሚችለው በታክስ ውሳኔ መጠን ላይ በመጨመር ወይም በመቀነስ ለውጥ የሚያመጣ ሲሆን ብቻ ሆኖ ለውጥ የማያመጣ በመሆኑ የማይታረም ስህተት ሲኖር ለታክስ ከፋዩ በጽሁፍ ይገለጻል።

## 15. የግምት ታክስ ስሌት ስህተትን ስለማረም

በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ቀጥሎ በተመለከተው መንገድ የሚታረም ይሆናል።

1. የግምት የታክስ ውሳኔ ላይ ስህተት አለበት የሚል ታክስ ከፋይ የግምት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ በተሰጠው ከ5 ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የታክስ ስሌቱን ላከናወነው ወይም ውሳኔውን ለሰጠው የሥራ ሂደት ጥያቄውን በጽሑፍ በማቅረብ ስህተቱ እንዲታረምለት ሊጠይቅ ይችላል።
2. የግምት ታክስ ስሌቱን የሰራው ሥራ ሂደት የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ከተሰጠ በኋላ በታክስ ስሌትና አወሳሰን ሂደት የተፈፀመ ግልጽና የማያከራክር ስህተት የፈፀመውን ባለሙያ ወይም የሌላ ባለሞያ አስተያየት ጭምር በማያያዝ ስህተቱ እንዲታረም የውሳኔ ሀሳብ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል።
3. የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ስህተቱ እንዲታረም ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በአግባቡ መመርመር ያለበት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የውሳኔ ሀሳብ ያቀረበለትን ባለሙያና የሥራ ሂደት አስተባባሪን ጠርቶ ማነጋገርና ማወያየት ይችላል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 በተገለጸው መንገድ ማጣራት የተደረገበት ጉዳይ ታክስ ከፋዩ ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጥያቄው ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

5. የቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ሊታረም የሚችል ስህተት አለመኖሩን በመግለጽ ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ ታክስ ከፋዩ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው ውሳኔው በደረሰው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለዋና መ/ቤት ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ዳይሬክቶሬቱም በ2 የስራ ቀናት ውስጥ እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ለአገር ውስጥ ታክስ ወይም ለሕግ ማስከበር ም/ዋና ዳይሬክተር ያስተላልፋል፡፡

6. በቀረበው ቅሬታ ላይ የአገር ውስጥ ታክስ ወይም የሕግ ማስከበር ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ለጥያቄው በቀረበ በ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ ውሳኔው በደረሰው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለዋና ዳይሬክተሩ በጽ/ቤቱ በኩል ሊያቀርብ ይችላል፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በተገለጸው መሰረት ጥያቄው በቀረበ በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት በኩል ለታክስ ከፋዩ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

9. ስህተቱ እንዲታረም ከተወሰነ፣ የታረመው ውሳኔ የመጀመሪያው ውሳኔ በሰጠው የሥራ ክፍል በኩል የተስተካከለ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጣል፡፡

10. ለታክስ ከፋዩ ተስተካክሎ የሚሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ቀደም ሲል የተሰጠው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ የተሻረ መሆኑን የሚገልጽና ስህተቱ በታረመበት ጊዜ ያለውን ቀንና ቁጥር የያዘ መሆን አለበት፡፡

11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እስከ 8 በተገለጸው ሂደት የሚያልፈው ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ 54(1) መሠረት በታክስ ውሳኔ ላይ በመደበኛ መንገድ ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜን ከመቆጠር የሚያስቀር አይሆንም፡፡

12. በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀርብ ስህተት የማረም ጥያቄ ጉዳዩ በቅሬታ ወይም በይግባኝ ወይም በፍ/ቤት ደረጃ ደርሶ የታየ ቢሆንም የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት ስለማሻሻል

### 16. የግምት ታክስ ስሌት ስለማሻሻል

በግምት የተወሰነ የታክስ ስሌት በአዋጁ አንቀጽ 28(1) ሐ መሰረት ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የሒሳብ መግለጫ ሳያቀርብ በመቅረቱ የግምት ስሌት ውሳኔ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር ከ 5 ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ቀጥሎ በተመለከቱ ሁኔታዎች ባለሥልጣኑ በራሱ አነሳሽነት አሻሽሎ ለመወሰን ይችላል።

1. የግምት ታክስ ስሌት ማስታወቂያ ከተሰጠ በኋላ የግዥ ወይም የሽያጭ መጨመርን የሚያሳይ መረጃ የተገኘ እንደሆነ፣
2. የመጀመሪያ የግምት ስሌት ውሳኔ በተጭበረበረ ወይም በተሳሳተ መረጃ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. በአዋጁ አንቀጽ 28(3)/ለ/ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ የተሻሻለው የግምት ታክስ ስሌት ለሁለተኛ ጊዜ ሊሻሻል የሚችለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጹ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው።

## ክፍል ስድስት

## የስጋት ታክስ ስሌት በግምት ስለሚወሰንበት ሁኔታ

### 17. የስጋት ታክስ ስሌትን በግምት ስለመወሰን

ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 27(1) መሰረት ቀጥሎ በተመለከተው መንገድ የስጋት ታክስ ስሌትን በግምት ሊወስን ይችላል።

1. ባለስልጣኑ የታክስ ከፋዩ ታክስ የመክፈል ሁኔታው ስጋት ላይ የሚጥል ተጨባጭ ማስረጃ ሲያጋጥምና ታክሱን በሒሳብ መዝገብ መሠረት መወሰን ያልተቻለ እንደሆነ የስጋት ታክስ ስሌትን በግምት ግብር አወሳሰን ሥርዓት የሚወሰን ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የስጋት ታክስ ስሌት በግምት ሊወሰን የሚችለው የሠንጠረዥ "ለ" እና "ሐ" ገቢ በሚያገኝ ታክስ ከፋይ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚወሰነው የግምት የስጋት ታክስ ስሌት እንደ አግባብነቱ የተርን ኦቨር ታክስ ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰላበት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የአሰራር ማኑዋል ስለማውጣት

ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት መሠረት አማካይ የቀን ገቢ ግምት የሚካሄድበትን የአሰራር ማኑዋል ያዘጋጃል፡፡

### 19. የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብዓት ስለማቀናነስ

1. በግምት የተወሰነው የምርት ውጤት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ ገቢ በቀጥታ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት የዋለ አቅርቦት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ግብይት የተከናወበትን ጊዜ መሠረት በማድረግ በታክስ አዋጁ በተቀመጠው ጊዜ ያሳወቀው እና ለአቅርቦቱ በታክስ ደረሰኝ ወይም ዲክላራሲዮን መሠረት የተከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ከግብዓት ታክሱ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው ቢኖርም በሒሳብ መዝገብ ተቀባይነት ያላገኘው የግብዓት ታክስ የተጠየቀበት ማስረጃ ግብይት የተፈፀመበት ስለመሆኑ አጣራጣሪና ማረጋገጥ የማይቻል ወይም ከሀሰተኛ ደረሰኝ ጋር የተገናኘ ከሆነ የግብዓት ታክሱ አይቀናነስም፡፡

3. ታክስ ከፋዩ የዘመኑን የሒሳብ መግለጫ አቅርቦ ኦዲት ሲደረግ በባለስልጣኑ በተደረገ ክትትል በተደጋጋሚ ደረሰኝ የማይሰጥ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የማይጠቀም መሆኑ ተረጋግጦ ገቢው በግምት የተወሰነ እንደሆነ በወርሃዊ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የገለጸው የግብዓት ታክስ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

## 20. ለኤክሳይዝ ታክስ መሠረት የሚሆነውን የማምረቻ ወጪ ስለመወሰን

1. የኤክሳይዝ ታክስን በግምት ለመወሰን ከሦስተኛ ወገን የሚገኝ የሽያጭ መረጃን ለምርቱ መጠን በማካፈል የሚገኘውን የማምረቻ ዋጋ ወይም ወጪ በመጠቀም የኤክሳይዝ ታክሱ ይወሰናል።
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈፃፀም የሚከተለውን ቀመር መጠቀም ይገባል።

$$ማወ = \frac{ሽዋ}{(1 + ት\ \%)\ (1 + ኤታ\ \%)}$$

$$ኤታ = ማወ \times ኤታ\%$$

<u>መግለጫ</u>

ማወ = ማምረቻ ወጪ

ሽዋ = የምርት ነጠላ መሸጫ ዋጋ/ግምት (unit price)

ት% = የተጣራ ትርፍ መተመኛ መቶኛ

ኤታ% = የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ

ኤታ = ተከፋይ ኤክሳይዝ ታክስ

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም የሚፈለገውን የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ለመወሰን የአንድ ነጠላ ምርት የማምረቻ ወጪን በወር ውስጥ በተመረተው ምርት መጠን በማባዛት የሚገኘውን ጠቅላላ ወርሃዊ የማምረቻ ወጪ በታክሱ መጣኔ በማባዛት ታክሱ ይወሰናል።
4. ግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ የያዘ ቢሆንም የኤክሳይዝ ታክስ መሠረት የሆነው የማምረቻ ወጪ ተለይቶ ባለመታወቁ ምክንያት ታክሱ በግምት አሰራር የተሰላ ከሆነ ከማምረቻ ወጪ ላይ ተቀናሽ መደረግ ያለበት የማሽነሪ የእርጅና ቅናሽ ታሳቢ መደረግ አለበት።

## 21. የማኑዋል ደረሰኝ ሲጠፋ ስለሚኖረው አሰራር

ማንዋል ደረሰኝ ሲጠፋ የሚኖረው አሰራርን በተመለከተ [illegible] የሚኖረው አሰራር

1. በታክስ ደረሰኝ አስተዳደር መመሪያ መሠረት ታክስ ከፋዩ ምንም ያልተሰራበት ደረሰኝ የጠፋበት መሆኑን ያስታወቀ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በሌላ መንገድ ደረሰኝ የጠፋበት መሆኑን ባስታወቀው ታክስ ከፋይ ስለመሰራቱ የሚገልጽ መረጃ ካላገኘ በስተቀር ታክስ አይወሰንበትም።

2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 የተገለፀው ቢኖርም የጠፋበትን ማንዋል ደረሰኝ ለባለስልጣኑ ስለመጥፋቱ ሲያሳውቅ የሚከተሉትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ታክሱ ይወሰናል።

ሀ.የጠፋው ደረሰኝ በከፊል የተሰራበት ከሆነ ቀሪ ካለው ከቀሪው ላይ የሚገኝ መረጃ፣ ወይም ቀሪ ከሌለው ታክስ ከፋዩ የተሰማራበት የንግድ ዘርፍ ባህሪ ከገዥዎቹ መረጃ የሚገኝበት ሲሆን ከገዥዎች የተገኘውን መረጃ፣ ወይም

ለ. ታክስ ከፋዩ የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ተመሳሳይ ዋጋና ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ በቆጠራ የተሸጠውን ዕቃ ብዛት በመለየት የሽያጭ ደረሰኝ የጠፋባቸውን ዕቃዎችን የሽያጭ ደረሰኝ ባላቸው ዋጋ እንደተሸጡ ተቆጥሮ በማባዛት የሚገኝ ይሆናል።

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ እና ለ በተዘረዘሩ መንገዶች የሽያጭ መረጃ ለማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ የታክስ ከፋዩ ዕቃ ወይም አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 3 መሠረት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መሰረት ታክሱ በግምት የሚወሰን ይሆናል።

መ. የጠፋው ደረሰኝ ሙሉ ለሙሉ የተሰራበት ደረሰኝ ከሆነ የሚወክለውን የሽያጭ መጠን ለማግኘት በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ ሀ የተገለጹ መንገዶችን በመከተል ታክሱ ይወሰናል።

3. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 የተገለፀው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ ምንም ያልተሰራበት ደረሰኝ የጠፋበት መሆኑን ሳያስታውቅ ባለሥልጣኑ በምርመራ ሂደት የደረሰበት እንደሆነ የተሰራበት ደረሰኝ እንደጠፋ ተቆጥሮ በተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ወቅት፣ ንግድ እና አካባቢ የሚገኝ የሦስት ታክስ ከፋይ ያስታወቀውን ወይንም የተወሰነበትን አማካይ ሽያጭ መሠረት በማድረግ ታክሱን በግምት ይወስናል።

## 22. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

በዚህ መመሪያ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ አስቀድመው የነበሩ አሰራሮችና ልማዶች ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ከሆኑ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

## 23. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመፅናቱ በፊት ተጀምረው እልባት ወይም ውሳኔ ያላገኙ የሚችሉ ጉዳዮች ቀደም ሲል ሲሰራበት በነበረው ሰርኩላሮች መሠረት ውሳኔ ያገኛሉ።

## 24. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሀምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ፣...... ቀን 2010 ዓ.ም

ዑመር ሁሴን

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር/ሚኒስትር

| ተ.ቁ | የየንግድ ዘርፍ የተጣራ ትርፍ፣ ያልተጣራ ትርፍ እና አማካይ የሥራ ቀናት ሠንጠረዥ-አባሪ አንድ | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የንግድ ዘርፍ | የተጣራ ትርፍ | ያልተጣራ ትርፍ | አማካይ ዓመታዊ የሥራ ቀናት |
| 1 | እህል፣ ጥራጥሬ፣ ቆሎና ቡላ ንግድ | 5% | 7.5% | 300 |
| 2 | የምግብ ዘይትና ፋጉሎ ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 3 | ቆዳና ሌጦ ንግድ | 10% | 15% | 210 |
| 4 | ክር፣ ጨርቃ ጨርቅ እና የጨርቃጨርቅ ውጤቶች ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 5 | ከረሜላ አምራች | 10% | 15% | 300 |
| 6 | መስታወት ሥራ ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 7 | በርበሬና ቅመማ ቅመም ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 8 | የመቃብር ሀዉልት ሥራ | 10% | 15% | 210 |
| 9 | አልጋ፣ ፍራሽና ደንገል መሥራትና መሸጥ | 10% | 15% | 300 |
| 10 | እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ንግድ | 10% | 15% | 210 |
| 11 | ጌሾና ብቅል ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 12 | ዕቃን በዕቃ ልዉዉጥ ንግድ | 10% | 15% | 150 |
| 13 | ከሰል ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 14 | ፀጉር ማስተካከልና የቁንጅና ሳሎን | 10% | 15% | 300 |
| 15 | የመኪና ወንበር ሰርቶ መሸጥና ማደስ | 10% | 15% | 300 |
| 16 | የልብስ ስፌት ብቻ | 10% | 15% | 300 |
| 17 | ጎማ ማደስ /ጎሚስታ/ ብቻ | 10% | 15% | 300 |
| 18 | ቴምብር በኮሚሽን መሸጥ | 10% | 15% | 300 |
| 19 | የጀበና ቡና ንግድ ብቻ | 10% | 15% | 300 |
| 20 | እህል ማበጠር | 10% | 15% | 300 |
| 21 | ሲጋቱራ ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 22 | ዶሮና እንቁላል ንግድ | 10% | 15% | 210 |
| 23 | የሰሌን ዘንባባና ቀርከሃ ዉጤቶች ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 24 | አሸንዳና ተጓዳኝ ሥራዎች | 10% | 15% | 300 |
| 25 | ቡና ንግድ | 10% | 15% | 300 |
| 26 | የግብርና ግብዓቶች አቅርቦት | 10% | 15% | 300 |
| 27 | የመጫንና ማውረድ አገልግሎት | 10% | 15% | 210 |
| 28 | የትራንስፖርት ተራ ማስከበር አገልግሎት | 10% | 15% | 210 |
| 29 | የስፖርት ዕቃዎች ንግድ | 11% | 16.5% | 300 |
| 30 | ስኳር አከፋፋዮች | 11% | 16.5% | 300 |
| 31 | የልብስ ንጽህና መስጫ/ላዉንደሪ/ | 11% | 16.5% | 300 |
| 32 | አዉሬ አሳዳኝ | 11% | 16.5% | 210 |
| 33 | የዕዳትና ገጸ ምድር ማስዋብ አገልግሎት | 12% | 18% | 210 |
| 34 | የጥበቃ አገልግሎት መስጠት | 12% | 18% | 300 |
| 35 | የዕርድ አገልግሎት | 13% | 19.5% | 210 |
| 36 | ማርና ቅቤ ንግድ | 13% | 19.5% | 300 |

| ተ.ቁ | የንግድ ዘርፍ | የተጣራ ትርፍ | ያልተጣራ ትርፍ | አማካይ ዓመታዊ የሥራ ቀናት |
|---|---|---|---|---|
| 37 | አትክልትና ፍራፍሬ ንግድ | 13% | 19.5% | 300 |
| 38 | ጥራኝ/ዝባድ/ ንግድ | 13% | 19.5% | 210 |
| 39 | የመኪና ዕቃ መለዋወጫ ንግድና የጋራዥ ሥራ | 13% | 19.5% | 300 |
| 40 | የእጣን ንግድ ብቻ | 13% | 19.5% | 300 |
| 41 | የጨዉ ንግድ | 13% | 19.5% | 300 |
| 42 | የወጥ ቤት፣ የገበታ ዕቃዎች /ድስት ሣህን፣ ማንኪያ፣ ብርጭቆ፣ ወዘተ---/ | 14% | 21% | 300 |
| 43 | ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጥና የምግብ ግሮሠሪ ንግድ | 14% | 21% | 300 |
| 44 | የባህል ዕቃዎች፣ ጌጣ ጌጥ እና የስጦታ ዕቃዎች ንግድ | 14% | 21% | 300 |
| 45 | የፋክስና ኢንተርኔት አገልግሎት መስጠት | 14% | 21% | 300 |
| 46 | ምግብ ማቅረብ | 15% | 22.5% | 300 |
| 47 | ብር፣ወርቅና ሌሎች የከበሩ ማዕድናት ሠርቶ መሸጥና አገልግሎት | 15% | 22.5% | 300 |
| 48 | ብረታ ብረትና የህንፃ መሣሪያዎች ንግድ | 15% | 22.5% | 300 |
| 49 | በጄኔሬተር የመብራት አገልግሎት መስጠት | 15% | 22.5% | 210 |
| 50 | እንጨትና አጠና ንግድ | 16% | 24% | 300 |
| 51 | ቃጫ፣ጆንያ እና ሌሎች ከረጢቶች ማምረትና መሸጥ | 16% | 24% | 300 |
| 52 | የዱቄት ንግድ | 16% | 24% | 300 |
| 53 | ፍሬን ሸራ ጥገና | 16% | 24% | 300 |
| 54 | ስዕል ሠርቶ ማሳየትና መሸጥ | 16% | 24% | 100 |
| 55 | የኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ንግድና ዕድሳት | 16% | 24% | 300 |
| 56 | የመሥሪያ ቤቶች ክበቦች | 16% | 24% | 260 |
| 57 | የግንባታ ሥራ ተቋራጭ | 16% | 24% | 300 |
| 58 | ጠቅላላ ኢንዱስትሪዎች/በፋብሪካ ደረጃ/ | 16% | 24% | 300 |
| 59 | የጫት ንግድ | 16% | 24% | 300 |
| 60 | ልዩ ልዩ ቅባቶችና ሽቶ ንግድ | 17% | 25.5% | 300 |
| 61 | የጥጥ ንግድ | 17% | 25.5% | 300 |
| 62 | ማተሚያ ቤት | 18% | 27% | 300 |
| 63 | የጫማና የጫማ ግብዓት ንግድ እና የጫማ ዕድሳት | 18% | 27% | 300 |
| 64 | የግንባታ ማዕድናት ማምረትና መሸጠ ንግድ | 18% | 27% | 300 |
| 65 | የህክምና አገልግሎት | 21% | 31.5% | 300 |
| 66 | የቆዳ ውጤቶችን መሥራት፣ መስፋትና ሠርቶ መሸጥ | 21% | 31.5% | 300 |
| 67 | ቀብር ማስፈፀምና ተዛማጅ ሥራዎች | 21% | 31.5% | 210 |
| 68 | ሌሎች አገልግሎቶች | 21% | 31.5% | 300 |
| 69 | የጽህፈት መሣሪያዎች፣ መጻሕፍት ቤት፣ መጽሐፈትና ጋዜጣ መሸጥ ሥራዎች | 22% | 33% | 300 |
| 70 | የኮምፒውተር ጽሕፈት፣ሕትመት፣ ፎቶ ኮፒና የመጠረዝ አገልግሎቶች | 22% | 33% | 300 |
| 71 | ሻማ ሠርቶ መሸጥ | 24% | 36% | 300 |

| ተ.ቁ | የንግድ ዘርፍ | የተጣራ ትርፍ | ያልተጣራ ትርፍ | አማካይ ዓመታዊ የሥራ ቀናት |
|---|---|---|---|---|
| 72 | ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችና ጨዋታዎች አገልግሎት | 25% | 37.5% | 300 |
| 73 | ሆቴሎች፣ቡና ቤቶችና ቁርስ ቤቶች | 25% | 37.5% | 300 |
| 74 | የኤሌክትሪክ ሊፍት ሥራና ዕድሳት | 25% | 37.5% | 300 |
| 75 | የጥብቅና አገልግሎት | 25% | 37.5% | 260 |
| 76 | የመኝታ አገልግሎት ብቻ /Pension/ | 26% | 39% | 300 |
| 77 | ነዳጅ ማደያዎች(ከማደያዎቹ ጋር የተያያዙ ካፍቴሪያዎች፣ሱቆችና ሌሎች አገልግሎቶችን ጨምሮ) | 26% | 39% | 300 |
| 78 | ፎቶ ግራፍ ማንሳትና ማጠብ | 26% | 39% | 300 |
| 79 | ሲጋራ በኮሚሽን አከፋፋይ | 26% | 39% | 300 |
| 80 | ሲኒማ ቤት | 27% | 40.5% | 300 |
| 81 | ሌሎች ዕቃዎችን በኮሚሽን መሸጥ | 27% | 40.5% | 300 |
| 82 | ሙዚቃና ቪዲዮ | 28% | 42% | 300 |
| 83 | መደበኛ ትምህርት መስጠት/ከአንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ/ | 28% | 42% | 300 |
| 84 | የሙያና የክህሎት ስልጠና መስጠት | 28% | 42% | 300 |
| 85 | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ ግንባታና ጠረጋ | 28% | 42% | 300 |
| 86 | ጎማ በኮሚሽን መሸጥ | 29% | 43.5% | 300 |
| 87 | የምህንድስና፣ ፕላንና ንድፍ ሥራ | 29% | 43.5% | 300 |
| 88 | የትርጉም አገልግሎት | 29% | 43.5% | 300 |
| 89 | የጉዞ ወኪል/አየር ትኬት መሸጥ/ና አስጎብኚ | 29% | 43.5% | 300 |
| 90 | ጉዳይ ማስፈፀምና የድለላ አገልግሎት | 30% | 45% | 300 |
| 91 | መዋዕለ ህፃናት (የግል) | 30% | 45% | 300 |
| 92 | የማስታወቂያ ሥራ እና የተለያዩ ዝግጅቶችን የማመቻቸት አገልግሎቶች | 30% | 45% | 300 |
| 93 | ልዩ ልዩ መገልገያዎችን ማከራየትና ፓርኪንግ አገልግሎት | 30% | 45% | 300 |
| 94 | የማታ ክበብ ብቻ | 30% | 45% | 300 |
| 95 | የምክር አገልግሎት /የግንባታ፣ የአስተዳደር፣ የፋይናንስ…ወዘተ/ | 30% | 45% | 300 |
| 96 | የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን /ማሽነሪዎችን/ ማከራየት | 30% | 45% | 300 |
| 97 | የሒሳብ ሥራ /ሒሳብ መዝጋት፣ ኦዲት/ | 30% | 45% | 300 |
| 98 | ተሽከርካሪ ማከራየት | 30% | 45% | 300 |
| 99 | ትራንዚተር /የጉሙሩክ አስተላላፊ/ | 30% | 45% | 300 |

## ደረጃ "ሀ"፣"ለ" እና "ሐ" በትራንስፖርት ንግድ ዘርፍ የሾፌር እና የረዳት ወርሃዊ ገቢ እና ግብር ሠንጠረዥ- አባሪ ሁለት

| ተ.ቁ. | የተሽከርካሪው ዓይነት | የቅጥር ገቢ እና ግብር | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የሾፌር ደመወዝ | ግብር | የረዳት ደመወዝ | ግብር |
| 1 | **የሕዝብ ማመላለሻ** | | | | |
| 1.1 | እስከ 5 ወንበር | 1,418 | 82 | | - |
| 1.2 | ከ6 - 12 ወንበር | 1,576 | 98 | 394 | - |
| 1.3 | ከ13 - 19 ወንበር | 1,576 | 98 | 473 | - |
| 1.4 | ከ20 - 23 ወንበር | 1,733 | 118 | 473 | - |
| 1.5 | ከ24 - 29 ወንበር | 1,733 | 118 | 630 | 3 |
| 1.6 | ከ30 - 34 ወንበር | 1,733 | 118 | 630 | 3 |
| 1.7 | ከ35 - 39 ወንበር | 1,812 | 129 | 630 | 3 |
| 1.8 | ከ40 - 44 ወንበር | 1,891 | 141 | 630 | 3 |
| 1.9 | ከ45 - 50 ወንበር | 2,206 | 188 | 788 | 19 |
| 1.10 | ከ51 ወንበር በላይ | 2,521 | 236 | 788 | 19 |
| 2 | **የደረቅ ጭነት መኪናዎች** | | | | |
| 2.1 | እስከ10 ኩንታል | 1,418 | 82 | 378 | - |
| 2.2 | ከ11 - 20 ኩንታል | 1,733 | 118 | 473 | - |
| 2.3 | ከ21 - 50 ኩንታል | 1,812 | 129 | 599 | - |
| 2.4 | ከ51 - 70 ኩንታል | 1,891 | 141 | 725 | 12 |
| 2.5 | ከ71 - 90 ኩንታል | 2,206 | 188 | 914 | 31 |
| 2.6 | ከ91 - 120 ኩንታል | 2,837 | 283 | 1,103 | 50 |
| 2.7 | ከ121 - 150 ኩንታል | 3,782 | 454 | 1,576 | 98 |
| 2.8 | ከ151 - 200 ኩንታል | 3,782 | 454 | 1,576 | 98 |
| 2.9 | ከ201 - 250 ኩንታል | 3,782 | 454 | 1,576 | 98 |
| 2.10 | ከ251 - 300 ኩንታል | 3,782 | 454 | 1,576 | 98 |
| 2.11 | ከ301 - 350 ኩንታል | 3,782 | 454 | 1,576 | 98 |
| 2.12 | ከ351 - 400 ኩንታል | 3,782 | 454 | 1,576 | 98 |
| 2.13 | ከ400 ኩንታል በላይ | 4,728 | 643 | 1,891 | 141 |
| 3 | **የፈሳሽ ጭነት መኪናዎች** | | | | |
| 3.1 | እስከ 11499 ሊትር | 3,152 | 330 | 1,261 | 66 |
| 3.2 | ከ11500 - 13000 ሊትር | 4,728 | 643 | 1,891 | 141 |
| 3.3 | ከ13001 - 25000 ሊትር | 4,728 | 643 | 1,891 | 141 |
| 3.4 | ከ25001 - 35000 ሊትር | 4,728 | 643 | 1,891 | 141 |
| 3.5 | ከ35001 - 45000 ሊትር | 4,728 | 643 | 1,891 | 141 |
| 3.6 | ከ45001 - 55000 ሊትር | 4,728 | 643 | 1,891 | 141 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3.7 | ከ55000 ሊትር በላይ | 4,728 | 643 | 1,891 | 141 |
| **4** | **የእህል ወፍጮ በአንድ ቋት** | | | | |
| 4.1 | በኤሌክትሪክ የሚሰራ | - | - | - | - |
| 4.2 | በናፍታ ኤሌክትሪክ የሚሰራ | - | - | - | - |
| 4.3 | በናፍታ ሃይል ብቻ የሚሰራ | - | - | - | - |
| **5** | **የእርሻ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች** | | | | |
| 5.1 | ኮምባይነር/ሐርቨስተር/ ማከራየት | 2,521 | 236 | 1,891 | 141 |
| 5.2 | ትራክተር/ለእርሻና ተዛማጅ ሥራ/ ማከራየት | 1,576 | 98 | 1,103 | 50 |

## መዝገብ ላልያዙ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" የትራንስፖርት ዘርፍ የንግድ ትርፍ ግብር መወሰኛ ሠንጠረዥ - አባሪ ሦስት

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ ዓይነት | ዓመታዊ ሽያጭ እና የንግድ ትርፍ ግብር | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተፈበረከ ከ1 - 15 ዓመት | | | | ከተፈበረከ ከ15 ዓመት በላይ | | | |
| | | የትርፍ መጣኔ | ዓመታዊ የሽያጭ መጠን | ግብር የሚከፈልበት ገቢ | ግብር | የትርፍ መጣኔ | ዓመታዊ የሽያጭ መጠን | ግብር የሚከፈልበት ገቢ | ግብ |
| 1 | የሕዝብ ማመላለሻ | | | | | | | | |
| 1.1 | ከ45 - 50 ወንበር | 11 | 500,641 | 55,071 | 7,384 | የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ | | | |
| 1.2 | ከ51 - 55 ወንበር | 11 | 522,196 | 57,442 | 7,858 | የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ | | | |
| 1.3 | ከ56 - 62 ወንበር | 11 | 581,190 | 61,025 | 8,575 | የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ | | | |
| 1.4 | 63 ወንበር እና ከዚያ በላይ | 10 | 630,714 | 63,071 | 8,988 | የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ | | | |
| 2 | የደረቅ ጭነት | | | | | | | | |
| 2.1 | ከ151 - 200 ኩንታል | 12 | 537,141 | 64,457 | 9,334 | የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ | | | |
| 2.2 | ከ201 - 250 ኩንታል | 10 | 729,578 | 72,958 | 11,459 | 10 | 620,143 | 62,014 | 8,773 |
| 2.3 | ከ251 - 300 ኩንታል | 9 | 841,702 | 75,753 | 12,158 | 9 | 715,446 | 64,390 | 9,318 |
| 2.4 | ከ301 - 350 ኩንታል | 8 | 994,335 | 79,547 | 13,107 | 8 | 845,185 | 67,615 | 10,123 |
| 2.5 | ከ351 - 400 ኩንታል | 7 | 1,336,692 | 93,568 | 16,612 | 7 | 1,136,190 | 79,533 | 13,103 |
| 2.6 | ከ400 ኩንታል በላይ | 6 | 1,702,560 | 102,154 | 19,186 | 6 | 1,447,016 | 86,821 | 14,925 |
| 3 | የፈሳሽ ጭነት | | | | | | | | |
| 3.1 | ከ25001 - 35000 ሊትር | 13 | 718,695 | 89,837 | 15,679 | 13 | 610,893 | 76,362 | 12,310 |
| 3.2 | ከ35001 - 45000 ሊትር | 11 | 924,808 | 97,105 | 17,671 | 10 | 786,086 | 82,539 | 13,855 |
| 3.3 | ከ45001 - 55000 ሊትር | 9 | 1,096,941 | 98,725 | 18,157 | 9 | 932,400 | 83,916 | 14,199 |
| 3.4 | ከ55000 ሊትር በላይ | 7.9 | 1,301,080 | 104,086 | 19,766 | 8 | 1,105,917 | 88,473 | 15,338 |